# ጉባዔ-አራት

# SERMON-4

# ከጉባዔ-ሦስት ለማስታወስ



አሮጌውን በር እናድስ!

## የትምህርቱ ዓላማ፤

፩ኛ-እግዚአብሔርን ማወቅ በራሱ ሕይወት ስለሆነ ለአምልኮ እንዲያግዘን፤

፪ኛ-የወልደ እግዚአብሔርን አምላክነቱን አዳኝነቱን ሰፋ አድርጎ ለማየት፤እና

፫ኛ-የቤተክርስቲያናችንን ዓለምን በወንጌል የመድረስ ራዕይ ለመደገፍ፡፡



## የትምህርቱ ዓላማዎች......በሌላ አገላለጽ

† የትምህርቱ ዓላማዎች (በዋናነት)

- የቀደመውን የእግዚአብሔርን ጥልቅ ሃሳብ መለስ ብሎ በማየት፤ እግዚአብሔር እዉነተኛ ፥ ሴይጣን ዉሸተኛ ለማለት፥
- መዳናችንን በማስረገጥ ፣ የድነትን ጽንሰ ሃሳብ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ለማስረዳት፤ ከተለመደዉ ዓይነትም ወጣ ብሎ የነገረ-ድነት ማጣቀሻ ጽሑፍ ለሚማርም ፥ ለሚያስተምርም ለማቅረብ፥
- ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት በቃል ስለምንሰጠው ምስክርነት ግንዛቤያችንን ለማስፋት ፥ እና
- ከዘፍጥረት 1-3 ያሉትን ዋና ሃሳቦች አጉልቶ በማሳየት ፤ የዘፍጥረት መጀመሪያው አምላክ ፣ የተቀረው የመጽሐፍ ቅዱስም ሁሉ አምላክ እንደሆነ በመግለፅ ላይ አነጣጥሯል።



† የትምህርቱ ዓላማዎች (ከግንዛቤ በማስገባት)፡

- ቀደም የተረዳነዉን እዉነት ለማጠናከር፥ የረሳነዉን ለማስታወስ፥ የተሳሳትነዉን ለማረም፥ ያላወቅነዉንም ለማሳወቅ ነው፤ ስለዚህ ሁላችንም ተማሪዎች ነን!
- ተናጋሪዉንና አነጋገሩን ሳይሆን የሚነገረዉን እዉነት ልክ እንደ ቤሪያ ክርስቲያኖች ከመጽሐፍ ቅዱስ አኳያ በመመዘን ከተቻለ ሁሉንም ፥ ካልሆነ ከፊሉን መቀበል ብልህነት ሲሆን፥ ሁሉንም አለመቀበል ደግሞ የራስ መብት ነዉ።



† ትምህርቱ የቤተክርስቲያኗን መሰረታዊ አስተምሮ ፍሬም የጠበቀ ቢሆንም፤ ከሁሉ በመሻል ለማስተማር ሳይሆን፤ በመዘጋጀትም ይሁን በማቅረብ ለመማር የሚሰጥ በመሆኑ፤

✓ ይህች አጥቢያ ቤተክርስቲያን ትምህርቱን የማረም መብት አላት።

✓ መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ የቃላት ግድፈቶችን በማረም ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

ማስገንዘቢያ

† አሮጌውን ቅጥራችን እናድስ ስንል፡-

- ✓እግዚአብሔር በዔድን ገነት የተናገረው ሁሉ እዉነት ነዉ፤ መነሻችንም ፥ መድረሻችንም እርሱ ነዉ። እያልን ነው።
- ✓አንድም ፤ የዘፍጥረቱ እግዚአብሔር የተቀረዉ መጽሓፍ ቅዱስ ሁሉ አምላክ ነው። ከዘመን በኋላም በልጁ በኩል የተናገረው ሁሉ እውነት ነው። እያልን ነው።



# ባለፈዉ ሳምንት





# የፍጥረት አጀማመር [ዘፍ1፡1-2፡3]



# እግዚአብሔር የፍጥረታት ፈጣሪ ነዉ።

ከሰዉ በቀር

ሁሉንም የፈጠረዉ

በቃሉ

ነዉ።



ፍጥረቱን ካለመኖር ወደ

መኖር፤ ከምንም ነገር

ወደ አንድነገር፤

ከማይታይም ወደሚታይ

አምጥቷቸዋል።



“ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል

እንደ ተዘጋጁ፥ ስለዚህም

የሚታየው ነገር ከሚታዩት

እንዳልሆነ በእምነት

እናስተውላለን።”

እንደሚል፡፡[ዕብ11³]



“መቼም ብዙ አማልክትና ብዙ ጌቶች አሉ፤

ነገር ግን በሰማይ ሆነ በምድርም ሆነ

አማልክት የተባሉ ምንም ቢኖሩ፥ለእኛስ ነገር

ሁሉ ከእርሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆንን

አንድ አምላክ አብ አለን፥ ነገር ሁሉም በእርሱ

በኩል የሆነ እኛም በእርሱ በኩል የሆንን

አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን።”

[1ቆሮ8⁵⁻⁶]

“ሁሉ በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም።”

[ዩሃ1$^{3}$]



“ሁሉን ያዘጋጀ ግን እግዚአብሔር ነው።”

[ዕብ3$^{4}$]



†ስለዚህም፣ በዚህ ዓለም የተደረጉ ግኝቶች ሁሉ አዲስ ሳይሆኑ በእግዚአብሔር ዘንድ ቀድሞውንም ታዉቀዉ፥ የተሰሩ፥ የተሰወሩ፥ አልያም ከእግዚአብሔር ፍጥረት ሥርዓት የተኮረጁ (imitate የተደረጉ) እንደሆኑ እናያለን፡፡



ምሳሌ፡-

- አዉሮፕላኖች ከወፎች፤
  - መርከቦች ከዓሶች፤
    - ሄሊኮፕተሮች ከበራሪ ፍጥረታት
      - ወዘተ ተኮርጀዋል።

እግዚአብሔር የጠለቀ ሚስጢሩን በፍጥረቱ አስቀምጧልና፤ የማይታየው የርሱ ባህርይ፥ የዘላለም ኃይሉ፥ ታላቅነቱ፥ አምላክነቱም ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሰሩት ታዉቆ ግልጥ ሆኖ ይታያል!![ሮሜ1[21]]

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።


…ያለመነም የጥበባት ሁሉ ምንጭ የሆነ እግዚአብሔር መኖሩን ከፍጥረት ይማራል!

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።


አንድም፤

ሰዉ እግዚአብሔር በፍጥረቱ የገለጠውንና የሰወረዉን ሚስጢር ማወቁ፤ ምን አይነት ድንቅ አምላክ እንደሆነ ከመረዳቱም ባለፈ የሚማረዉ እጅግ ድንቅ ትምህርትም አለ።

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።


ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስም አብዛኛው ትምህርቶቹን በምሳሌ አስደግፎ ማስተማሩ ፤ የተገለጡ ትንቢቶችም በራእዮችና በምሳሌዎች መሆናቸዉን፤ ላስተዋለዉ ሁሉ እግዚአብሔር የጠለቀ ሚስጢሩን በፍጥረት ሥራዓቱ እንዳደረገ ይገባዋል።

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።




# ቀን አንድ፡- በመጀመሪያ እግዚአብሔር[ዘፍ1[1]]





ከሁሉም ቀድሞ ፤ ዘመናትም ከመጀመራቸዉ በፊት እግዚአብሔር አለ፡፡ የዓለማት ፈጣሪ እግዚአብሔር፤ መጀመሪያ የሌለው መጀመሪያ፥ መጨረሻም የሌለዉ መጨረሻ (አልፋና ዖሜጋ)፤ ሁሌም ያለ÷ ሁሌም ዘለሳማዊ አሁን የሆነ፤ በራሱ የነበረ፥ ያለ፥ የሚኖርም አምላክ (ያህዌ) ነው፡፡





ስለዚህ ምንም መጀመሪያ ይሁን መጨረሻ የሌለውን፣ በራሱ የሚኖር አምላክን መጀመሪያ ማወቅ አይቻልምና፤ እንደ መጽሐፍ ቅዱሱ የመጀመሪያ ዓረፍተ-ነገር "እግዚአብሔር በመጀመሪያ"

ብሎ ከመቀበል ውጭ ሌላ

አማራጭ የለም!



እንግዲህ.....

በመጀመሪያ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሰማይንና ምድርን ፈጠረ፣ የሚለው የዕብራይስጡ 'ኤሎሂም' በነጠላ ግስ ብዙ ቁጥር ማሳየቱ፤ ሥላሴ በፍጥረት ሥርዓት በእኩል ተሳታፊ እንደነበሩ ያሳያል!

- ስለ አብና ወልድ [1ቆሮ8$^{5-6}$]፤
- ስለ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ [ዘፍ1$^{2}$፣ኢዮ33$^{4}$፣ መዝ 104$^{30}$]፡፡

# የሆነ ሆኖ የፍጥረት ስርዓቱ በዋናነት የተመራዉ በወልድ ነው፡፡

[ምሳ $8^{22-31}$ ከ1ቆሮ$1^{24}$ ጋር ያነጻጽሩት ፣ ዕብ$1^{2}$]

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።



# ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጥረትን የፈጠረ ብቻ ሳይሆን አሁንም አጽንቶ የያዘዉ እርሱዉ ነዉ!

[ቆላ$1^{16}$]

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።





” እስካሁን ያየነዉ በዚህ በዘፍ $1^{1}$ ያለዉን መጀመሪያ፣ ከፍጥረቱ በፊት የነበረውን መጀመሪያ የሚያመላክት እንደሆነ ነበር፡፡”

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።





” መጽሐፍ ቅዱሳችን ሌላ የመጀመሪያ ፅንሰ ሃሳብ እንዳለ በሀዲስ-ኪዳን መግቢያ ላይ ይገልጻል፡፡”

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

† ሌላኛው "መጀመሪያ" ዮሃንስ ወንጌላዊዉ የሚለው መጀመሪያ ነው፡፡ [ዮሃ1 1-5] ይኸኛው መጀመሪያ 'ወልድ' በመለኮታዊ ክብሩ ከአብ ጋር ያለውን ዘላለማዊ አንድነቱን የሚገልጽ ነዉ፡፡

➢ በዚህም ይህ በእግዚአብሔር ዘንድ በመጀመሪያ የነበረው፥ እግዚአብሔር የሆነው፥ የእግዚአብሔር ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ሁሉ በርሱ የሆነ፥ ከሆነውም አንዳች እንኳ ያለርሱ የልሆነው አምላክ እንደሆነ ይገባናል፡፡



† ይህ በእግዚአብሔር ዘንድ በመጀመሪያ የነበረው ቃል፥ ይህ ፍጥረትን ያስገኘው ቃል፤ ሁሉ በእርሱ ሆኗልና፥ ከሆነውም አንዳች እንኳ ያለእርሱ አልሆነምና፤ በእርሱ ሕይወት ስለነበር፥ ሕይወትም የሰው ብርሃን ስለሆነች፤ ቃል ሥጋ ሆኖ፥ ፀጋንና እውነትንም ተሞልቶ፣ በእኛ በማደር፣ ሕይወትን ሰጥቶናል፡፡ [ዩሃ1 1-14]



† ይኸዉ ወንጌላዊ ሓዋሪያ

ከመጀመሪያ የነበረው ዘላለማዊ አምላክ እግዚአብሔር፣ በስጋ እንደተገለጠ፤ በአብ ዘንድ ከመጀመሪያው የነበረው ሕይወት፣ ሰዉ እንደሆነ፤ እርሱም በአይኖቹ እንደየዉ፥ በእጆቹ እንደዳሰሰዉ፥ በጆሮቹም እንደሰማዉ፤ በዋለበት እየዋለ፥ ባደረበትም እያደረ ከእግሮቹ ሥር እንደተማረ በመልዕክቱ ገልጧል፡፡ [1ዮሃ1 1-4]



በዚህም የዘላለም ሕይወት፤ የታየው፥ የተዳሰሰወ፥ የተሰማዉ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ፤ መገለጡም አዳም ቅጠል በልቶ ከእግዚአብሔር ጋር በመጣላቱ፣ በመሞቱም፤ በስሙ ለሚያምኑ ሁሉ ሕይወትን ለመስጠት እንደሆነ እናያለን፡፡ በርሱ ሕይወት ነበረች፥ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች። ይላልና፡፡

፨ ሚስጢሩ"የዛሬ 2000 ዓመት የዘላለም ሕይወት በሥጋ ተገልጦ፤

"የምንነቀም ብንሆን፥ የምናንቀላፋም ብንሆን ከእርሱ ጋር አብረን በሕይወት እንኖር ዘንድ፣ ስለ እኛ ሞተ፡፡" [1ተሰ5$^{10}$]



አንድም፤ የዘላለም ሕይወት በሰውም ይሁን በመላእክት ፀሎት የማይታደል፥ በመመጽወትም ይሁን በመያም ዓይነት ስርዓት የማይመጣ ፥ አሊያም የሆነ ሀይማኖታዊ Process ሳይሆን፤ የዘላለም ሕይወት ራሱጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነና፤ የሚገኘዉም የድንግል ማሪያምን ልጅ ካለወንድ ዘር በድንግልና ተጸንሶ የተወለደዉ እርሱ የሰዉ ልጆች ሕይወት ነዉ። ብሎ በማመን ብቻ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡



እንግዲህ . . . . . በመጀመሪያ እግዚአብሔር ከሚለዉ አስተምሮ መሰረተ ሃሳብ አኳያ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ማመን ወይም ክርስቶስን መቀበል ማለት በራሱ ምን ማለት ነዉ???ብለን ጠይቀን



መልሱን መጀመሪያ የነበረው፥

ሰማይና ምድርንም የፈጠረው እግዚአብሔር፤ አዳም በመበደሉ የተነሳ የሰው ዘር ሁሉ ስለሞተ፤ እርሱ ደግሞ የሰው ሕይወት ስለሆነ፤ ከንፅህት፥ ቅድስት፥ ድንግል ማርያም ያለወንድ ዘር ተወልዶ፤ ፍጹሙ አምላክ፣ፍጹም ሰዉ ሆኖ፥ በሥጋም ተገልጦ የተዳሰሰዉ፥ የታየውም የዘላለም ሕይወት እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ከእርሱ ጋር በሕይወት እኖር ዘንድ ሞቶልኛል፥ እርሱ ሕይወቴም፥ ትንሣኤዬም ነው። ብሎ ማመን ነው፡፡ "

እርሱም የሰጠን ተስፋ ይህ የዘላለም ሕይወት ነውና። [1ዮሃ2$^{25}$፣ዩሃ5$^{26}$፣ራዕ20$^{15}$]

ብለን ነበር፡፡